# የኦዲት ግኝት መረጃ አመላካች

**መረጃ ሰጪው: -** የግብርና ትራንስፎርሜሺን ኤጀንሲ

**ኦዲት ተደራጊ: -** የግብርና ትራንስፎርሜሺን ኤጀንሲ

**ኦዲት የተደረገው የበጀት ዓመት: -** የ2012 4ኛ ሩብ ዓመት

**የኦዲት አካባቢ: -** የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት

**የኦዲት ግኝት: -**

## 1. ደረጃውን ባልጠበቀ የውል ስምምነት መሰረት ተፈጽሞ የተገኘ የብር 256,956.88 ግዥ፤

### 1.1 ሁኔታ: -

ኤጀንሲው ለተሽከርካሪዎቹ የነዳጅ፣ የዘይትና ቅባት ግዢን ማድረግ ይችል ዘንድ ከጎልድ ማርክ ትሬዲንግ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጋር የውል ስምምነት በማድረግ የብር 256,956.88 ለተሽከርካሪዎች የነዳጅ ግዢ የፈጸመ ቢሆንም፤

- በኤጀንሲው በኩል የውል ስምምነቱ የተፈረመው ህጋዊ ሥልጣን/ውክልና በሌለው በመ/ቤቱ የቀድሞው የሎጂስቲክስ ቡድን መሪ መሆኑ፣
- ግዢው የተፈጸመው ደረጃውን ባልጠበቀ የውል ስምምነት መሰረት መደረጉ፤ ለምሳሌ ውሉ የተፈጸመበትን ቀን እና የሚጸናበትን ጊዜ የማያሳይ በመሆኑ እንዲሁም፣
- ጎልድ ማርክ ትሬዲንግ ማህበር የተመረጠበት መስፈርት በግልፅ የማይታወቅ መሆኑ::

ለዚህም በ2012 በጀት ዓመት አራተኛ ሩብ ዓመት ክፍያ የተፈጸመባቸውን የነዳጅ ግዢዎች እንደሚከተለው በሰንጠረዥ አቅርበናል::

| ተ/ቁ | የማጠቀሻ ቁጥር | የገንዘቡ ልክ | ነዳጅ የተሞላበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1 | 199 | 9, 466.26 | 1/4/2020-03/4/2020 |
| 2 | 198 | 5, 1730.78 | 16/3/2020-31/3/2020 |
| 3 | 207 | 3, 463.50 | 16/4/2020-30/4/2020 |
| 4 | 246 | 29, 497.34 | 1/3/2020-15/3/2020 |
| 5 | 247 | 32, 480.76 | 16/1/2020-31/1/2020 |
| 6 | 250 | 27, 210.64 | 1/1/2020-15/1/2020 |
| 7 | 248 | 36, 580.13 | 16/2/2020-29/2/2020 |
| 8 | 251 | 19, 392.20 | 1/2/2020-15/2/2020 |
| 9 | 249 | 47, 135.27 | 16/12/219-31/12/2019 |
| ድምር | | **256, 956.88** | |

1.2 **መስፈርት፤** የፌደራል መንግስት የግዢ አፈጻጸም መመሪያ::

1.3 **መንስኤ፣** የፌደራል መንግስቱን የግዢ አፈጻጸም መመሪያ በሚገባ አለመረዳት፤ የተደረገው የውል ስምምነት ትክክለኛና ተቀባይነት እንደሌለው አለመገንዘብ::

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Agricultural Transformation Agency

1.4 **የሚያስከትለው ጉዳት፣** ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፣ ሂሳቡ ተቀባይነትን ሊያጣ ይችላል፡፡

## 2. ደጋፊ ማስረጃዎች ሳይሟሉ ተመዝግበው የተገኙ ብር 1,324,922.30 የወጪ ሂሳቦች፡፡

2.1 **ሁኔታ፤** ለናሙና ከተወሰዱት ሂሳቦች መካከል በድምሩ የብር 1,324,922.30 ወጪዎች አስፈላጊ የሆኑ ደጋፊ ማስረጃዎች ከክፍያ/ከምዝገባ ቫውቸሮች ጋር አለመያያዛቸው፤ ይህም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

<u>**ደጋፊ ማስረጃዎች ሳይሟሉ ተመዝግበው የተገኙ የወጪ ሂሳቦች**</u>

| ተ/ቁ | የማጣቀሻ ቁጥር | የወጪ ኮድ | የክፍያው ምክንያት | የገንዘቡ ልክ በብር | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 29 | 2311203 | ለህንጻ ግንባታ-ለመኖሪያ ላልሆነ | 302,143.68 | |
| 2 | 213 | 2211107 | ነዳጅና ቅባት | 101,860.66 | |
| 3 | 29 | 2211102 | የቢሮ ቁሳቁስ | 55,542.82 | |
| 4 | 29 | 2211102 | የቢሮ ቁሳቁስ | 48,825.55 | |
| 5 | 29 | 2211102 | የቢሮ ቁሳቁስ | 43,793.63 | |
| 6 | 45 | 2211110 | የእርሻ፣ደንና የባህር ግብዓቶች (Agriculture, forestry, and marine Inputs) | 160,000 | |
| 7 | 45 | 2211110 | የእርሻ፣ደንና የባህር ግብዓቶች (Agriculture, forestry, and marine Inputs) | 80,000.00 | |
| 8 | 5 | 2211110 | የእርሻ፣ደንና የባህር ግብዓቶች (Agriculture, forestry, and marine Inputs) | 80,000.00 | |
| 9 | 27 | 2211110 | የእርሻ፣ደንና የባህር ግብዓቶች (Agriculture, forestry, and marine Inputs) | 101,796.00 | |
| 10 | 27 | 2241108 | የስልክ ወጪዎች | 14,655.48 | |
| 11 | 27 | 2241108 | የስልክ ወጪዎች | 14,575.64 | |
| 12 | 47 | 2211102 | የቢሮ ቁሳቁስ | 50,834.80 | |
| 13 | 24 | 2221102 | የቢሮ ቁሳቁስ | 79,131.27 | |
| 14 | 24 | 2221103 | ለቢሮ መስተንግዶ | 28,834.94 | |
| 15 | 30 | 2211101 | ለደንብ ልብስ | 69,999.90 | |
| 16 | 30 | 2211101 | ለደንብ ልብስ | 2,599.00 | |
| 17 | 20 | 2231107 | ጥገናና እድሳት-ተሽከርካሪና ሌሎች መጓጓዣ | 44,750.00 | |
| 18 | 203 | 2211107 | ነዳጅና ቅባት | 45578.93 | |
| ድምር | | | | 1,324,922.30 | |

2.2 **መስፈርት፤** የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 9፡፡

2.3 **መንስኤ፣** የሂሳብ መረጃዎች በERP የኮምፒውተር ምዝገባ ስርዓት ተመዝግበው ወደ IFMIS ሲዛወሩ ከመክፈያ ሰነዶች ጋር ተያይዘው የተቀመጡት ዋና (ኦሪጂናል/ ደጋፊ ሰነዶችም ፋይል ተደርገው በአግባቡ አለመቀመጣቸው፤ ከመንግስት በጀት ሙሉ ለሙሉ ክፍያቸው ለተፈጸሙ ወጪዎች ደጋፊ ሰነዶቹ ከመክፈያ ሰነዱ ጋር መያያዝ እንዳለባቸው አለመረዳት፡፡

2.4 **የሚያስከትለው ጉዳት፣** ክፍያው ተቀባይነትን ላያገኝና ተጠያቂነትንም ሊያስከትል ይችላል፡፡

## 3. የብር 904,959.93 የወጪ ሂሳቦች የተያያዙት ደጋፊ ሰነዶች ፎቶ ኮፒ መሆናቸው፡፡

3.1 **ሁኔታ፤** ለናሙና ከተወሰዱት የወጪ ሂሳቦች መካከል በድምሩ ብር 904,959.93 ዋናው/ኦሪጂናል ደጋፊ መረጃ መያያዝ ሲገባ ፎቶኮፒያቸው መያያዙ፤ እነዚህም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

<u>**በፎቶ ኮፒ ደጋፊ ሰነዶች የተከፈሉ የወጪ ሒሳቦች**</u>



The Federal Democratic Republic of Ethiopia Agricultural Transformation Agency